ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

ለቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት አባላትና ቤተሰቦቻቸዉ በያሉበት
እንዲሁም ለሚመለከታቸዉ ተባባሪ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን

ጉዳዩ ፣ በነሀሴ 01/2014 እ,ኤ,አ በSBS(ኤስ,ቢ,ኤስ) የአዉስትራሊያ የአማሪኛ ጣቢያ ስለማህበራችን አስመልክቶ የተሰጠዉ ቃለ ምልልስ በሚመለከት

***ዉድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን***

በቅድሚያ ማህበራችንን ለማቋቋምና ብሎም ከተቋቋመም በኃላ እየሰጣችሁን ያለዉን ድጋፍና አስተዋፅኦ ከልባችን እያመሰገንን ለወደፊትም ብሆን በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥል ሙሉ እምነታችን ነዉ።

ዛሬ ሳንወድ በግድ ይህንን መግለጫ ለማዉጣት ያስገደደን በቅርቡ በሻለቃ ደምሴ ዮሐንስ በSBS የአዉስትራሊያ የአማሪኛ ሬዲዮ ጣቢያ የተሰጠዉን ፍጹም ትክክለኛ ያልሆነና የተሳሳተ መግለጫ ዝም ብለን ብናልፍ ትክክል ነዉ ብለን እንደተስማማን ስለሚያስቆጥርብን ነዉ።

ዉድ ወገኖቻችን

አበዉ እንደሚሉት,,,, «እዉነትና ንጋት እያደር መጥራቱ ,,,,,» ይባላል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ቡዙ ጉዳትና እልቂትን ያስከተሉ ጦርነቶችን ብንመለከት ጠላቶቻችን በዉጊያ ስልት ወይም በሰዉ ኃይል የበላይነትን አግኝተዉ ሳይሆን ከወገን ጋር አብረዉ ከመስራት ይልቅ ጊዚያዊ ጥቅምና ስም ለማግኘት ሲሉ ብቻ ከጠላት ጎራ በተሰለፉ ከዳተኞች እርዳታ ነዉ። ለዚህ ምሳሌ መጥቀስ አያስፈልግም። በወቅቱ በዚህ ባሳለፍነዉ ሃያ ሶስት ዓመታት ዉስጥ በሀገራችን በርካታ የተሳሳተና ትክክለኛ ያልሆኑ ታሪኮች ተደጋግመዉ እየተነገሩ ብዙ ችግር ዉስጥ የገባን ስለሆነና በወቅቱም እነዚህ ትክክለኛ ያልሆኑ ነገሮች ባለመጋለጣቸዉ እዉነት እየመሰሉ እንደ እዉነት ስለሚታዩ እኛም ይህንን ፍጹም የተሳሳተ የመኮንኑን ትክክለኛ ያልሆነ ንግግር በወቅቱ ካላጋለጥን ወደ ማህበራችን ገና ለመምጣት እየተዘጋጁ ያሉትን የቀድሞ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት አበላት አላስፍላጊ ዉዥንብር ዉስጥ ሊከት ስለሚችል ይህንን የተሳሳተ ነገር ለጉዳዩ ባለቤት የማሳወቅ ግዴታ ስለአለብን ፦ መኮንኑ ስለሰጡት ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫም ሆነ መኮንኑ ላስቬጋስ ከተማ ላይ መስርተነዋል ስለሚሉት ማህበርና እኛ ቀደም ሲል በግንቦት 28/2014 እ,ኤ,አ መተዳደሪያ ደንብ አዉጥተን ስለመሰረትነዉ ማህበር ልዩነት በግልፅ ለማስቀመጥ እንወዳለን።

ጉዳዩ እንደሚከተለዉ ነዉ።

መኮንኑ በSBS የሬድዮ ጣቢያ ጋዜጠኛ ፦ «ይህ የእኛ የቀድሞ የጦር ኃይሎች ዓለም አቀፍ ማህበር በህጋዊነት ቀደም ብሎ መመስረቱን በመጥቀስ ለምን እሳቸዉና አብሮአቸዉ ያሉት ግለሰቦች ላስቬጋስ ከተማ ላይ ሌላ ማህበር ለማቋቋም እንደፈለጉ ጥያቄ ሲያቀርቡላቸዉ ፣

መኮንኑ 1ኛ ይህ ከሃያ ሶስት ዓመት በኃላ በግንቦት 28/2014 በህጋዊነት የተመሰረተዉ የቀድሞ የጦር ኃይሎች ዓለም አቀፍ ማህበር በችኮላ የተመሰረተ እንደሆነ፦

2ኛ በአሁኑም ሰዓት ደግሞ በፀፀት ላይ እንደምንገኝና ወደእነሱ ለመምጣት እንደወሰንና በቅርቡም ወደ እነሱ እንደምንጠቃለል

3ኛ በተደጋጋሚ እሳቸዉና አብረዋቸዉ ላስቬጋስ ከተማ ያቋቋሙት ማህበራቸዉ ከዘረኝነትና ከሃይማኖት ልዩነት የሌለበት ወዘተ,, እንደሆነ

4ኛ በእሳቸዉ የሚመራዉና አቋቁሜዋለሁ የሚሉት ማህበር ሲመሰረት በምስረታዉ ላይ በርካታ የሰራዊቱ አባላትና የሰራዊቱ ቤተሰቦች እንደተገኙ ወዘተ,,,

5ኛ አልፎ ተርፎም የሃይማኖት መሪም እንደተገኙና ,,,ወዘተ,,,,ወዘተ,,,,,,ብለዋል።

***ዉድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን***

1ኛ እኛ ሃያ ሦስት ዓመት ሙሉ ማህበር ሳናቋቁም ያለስማችን ስም፣ ያለ ስራችን ስራ ተሰጥቶን አንገታችንን ድፍተን መቀመጣችን፣ በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ላይ ስለተፈፀመዉና እየተፈፀመ ሰላለዉ ኢሰብአዊ ድርጊትና የሰብአዊ መበት ጥሰትን ባለመጠቆማችንና ባለማጋለጣችን ቢቆጨንም ሌሎችም ለምን ይህን ያህል ጊዜ ወሰደባችሁ ቢሉንም እኛ ከዚህም በመነሳት አሁንም ቢዘገይም አንተዉም፣ ባለን አቅማችን ተነስተን የምንችለዉን እናደርጋለን ብለን ስንነሳ እኚህ መኮንን ደግሞ አሁን እኛ ይህንን በማድረጋችን ከቸኮልናባቸዉ ሌላ ስንት ዓመት ከዚህ በኃላ መጠበቅ እንዳለብን አልነገሩንም? እኛስ ከዚህ ቀደም ለሃያ ሦስት ዓመታት ማህበር ስላልነበረን ለማቋቋም ቸኮልን። እሳቸዉ ግን ይህ ማህበር በህጋዊነት መመስረቱን እያወቁ ለምን በእሳቸዉ የሚመራ ሌላ ተለጣፊ ማህበር ለማቋቋም እንደቸኮሉ አልነገሩንም።

2ኛ እኛ እንደተፀፀትን ገልፀዋል። እኛ ይዘን የተነሳነዉ ባለ ስምንት ነጠብ ዓላማ ሁሉም ሰዉ ሊግባዉ በሚችል ቋንቋ እንደተከፈተ መፅሃፍ በግልጽ አሰቀምጠናል። ይዘን የተነሳነዉ ዓላማ መስዋዕትነት ከፍለዉ ለአስራ ሰባት ዓመታት ከዉጪ ወራሪና ከሻቢያና ወያኔ ጋር ታግለዉ የወደቁትን ጅግኖቻችንን ለመዘከር፣ በህይወት ያሉትንም ጀግኖች ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ሰብአዊ መብታቸዉን ለማስከበር ፣ ታሪካችንን ለትዉልድ አሳልፎ ለማስረከብ ብሎም ሀገራችን ብትፈልገን ልንደርስላት እንድንችል ለማስገንዘብ ስለሆነ ይሄ የሚያኮራን እንጂ የሚፀፅተን አይደለም። ብንፀፀትም እስከ ዛሬ ይህንን ያለማድረጋችን ነዉ። ከዚህ ዉጪ አሁንም እኛ የምናምነውና የሚፀፅት ስራ ቢኖር ቀደም ብሎ በህግ የተቋቋመ ማህበር እያለ ከሃገርና ከሰራዊቱ ፍቅር ከማስቀደም ይልቅ የድርጅትና የገንዘብ ፍቅር በልጦባቸዉ ተለጣፊ ድርጅት ማቋቋማቸዉ ነዉ።

3ኛ በተደጋጋሚ በንግግራቸዉ መሃል የዘረኝነትና የሃይማኖት ልዩነት እንደሌለ ተናግረዋል። «ምን ያለበት ምን አይችል»ካልሆነ በስተቀር እኛ መነሻችንም መድረሻችንም ኢትዮጵያዊነት እንደሆነ በግልፅ አስቀምጠናል። የቀድሞ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት አበላት ሃገራችንን ያገለገልነዉ ኢትዮጵያን ብለን ነዉ። ዛሬም እንደዚሁ እኛ የብሄረሰብና የጎሳ ሰፈር ዉስጥ አልገባንም። ስለ ሃይማኖት ልዩነት አላነሳንም። ለምን እንደደጋገሙት እንኳ እዉነቱን ሳይነግሩን ነዉ ያለፉት። ሌላዉ መኮንኑ የሃይማኖት ልዩነት እንደማያድርጉ ያለማፈር አፋቸዉን ሞልተዉ ነግረዉናል። ወዲያዉ ደግሞ ዞር ብለዉ በምስረታችን ላይ የታወቁ አባታችን ብፁእ አቡነ መቃሪዮስ መገኘታቸዉን በኩራት ስነግሩን ተሰምተዋል። ለመሆኑ የአንድ ኃይማኖት አባት ብቻ መጋበዝና ሌላዉን ለምን እንዳገለሉ እንኳን አልገለጹልንም። መቼም «የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም» ይባል የለ። ሌላው መኮንኑ ስለ ምሥራቁ ፣ስለ ደቡብና ስለ ምዕራብ ጦርነት በሰፊዉ ሲያወሩና ሲያብራሩ የህወሃት ፈጣሪ አባትና የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ስለሆነዉ ሻቢያ አንዴ እንኳን ደፍረዉ ለመናገርና ስም ለመጥራት እንኳ እንደተሳናቸዉ እንዲያዉ ሰሜን በሚል ብቻ እንዳለፉት ሁላችንንም በጣም አስደምሞናል።

4ኛ በእሳቸዉ የሚመራዉና አቋቋምኩት የሚሉት ማህበር ሲመሰረት , በምስረታዉ ላይ በርካታ የሠራዊቱ አባላትና ቤተሰቦች እንደተገኙ ወዘተ,,,, ብለዋል።
በቅድምያ ለምን ላስ ቬጋስ ከተማ እንደተመረጠና ማን ወጪዉን ፋይናንስ አድርጎ እንደሸፈነ ቢገልፁልን መልካም ነበር። ነገር ግን አልሆነም። ስለ ምስረታዉ ሙሉ ቪድዮ ባያሳዩም እኛ ባልን ቪድዮ ቅጂ እነማን እንደተገኙ ፣እነማን ማንን ድርጅት ወክለዉ እንደተገኙ ፣ የየትኛዉ ድርጅት ተወካይ የክብር እንግዳ እንደነበሩ ሁላችንም የምናዉቀዉ ነዉ። በዚህ ጉዳይ ዙርያ ብዙ ማለት ይቻል ነበር ፣ ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስነዉ «እዉነትና ንጋት እያደር ስለሚጠራ»,,,, ለጊዜዉ ብዙ ከማለት እንቆጠባለን።

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**



***ዉድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን***

ስለ መኮንኑ ትክክለኛ ያልሆነ ቃል በአጭሩ ይህንን ካልን በኃላ ስለ እኛ በግንቦት 28/2014 እ,ኤ,አ, ለመጀመሪያ ግዜ ስለተመሰረትነዉ ማህበራችንና መኮንኑ በቬጋስ ከተማ ላይ መስርተነዋል ስለሚሉት ማህበር መሰረታዊ ልዩነት ለማያዉቁ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት አባላት እንዲሁም ቤተሰቦችና ደጋፊ አባሎች ሁሉ ለወደፊቱም ወደማህበራችን ለሚመጡ አባላትና ኢትዮጵያዊያን በሙሉ አላስፈላጊ የሆነ ቢዥታ እንዳይፈጥር ከዚህ እንደሚከተለዉ ያለዉን መሰረታዊ ልዩነት እናስቀምጣለን።

በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ይሄንን የቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ዓለም አቀፍ ማህበር በይፋ ከማቋቋማችን በፊት ላልፉት ሃያ ሦስት ዓመታት በዝህ ጉዳይ ላይ እንደማንኛዉም የጦር ኃይሎች አባላት ስለተፈጸሙብን ግፍና ሰማዕት የሆኑት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ስለከፈሉት መስዋዕትነት በከንቱ እንዳይቀር በሚል ሁላችንም በዚህ ጉዳይ ዙርያ ላይ ሲከነክነን የነበረ ነገር ሲሆን በተለይ ላለፉት ሁለት ዓመታት ደግሞ በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢና በደላስ አከባቢ የምንገኝ የቀ/የኢ/የጦ/ኃይ/የፖ/ ሠራዊት አባላት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ብዙ ስንመክርበት የነበረ ጉዳይ እንደነበረ ቀጥሎም ይህንን ማህበር ለማቋቋም በሂደት ላይ እንዳለን በአጋጣሚ በኮንፍረንስ ኮል አማካኝነት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ዉይይት ሲደረግ ስለነበር እኛም በዚህ ኮንፍረንስ ኮል ላይ የተሳተፍን ሲሆን ሊስሩ የሚገባቸዉን ሲራዎች በመነጋገር ለጊዜዉ የሚያስተባብር ጊዚያዊ ኮሚቴ ተመስርቶ የመተዳደሪያ ደንብ አዉጥተን ማህበሩን ለማቋቋም ዉይይት ላይ እያለን፤ እኚሁ መኮንንና ከእሳቸዉ ጋር አሁን ቬጋስ ከተማ ማህበር አቋቋምን የሚሉት ሌሎች አምስት ግለሰቦች

፩ኛ,ገና ከጅምሩ የሻቢያ ስም እንዳይጠራ , የኤርትራ መንግስት ብላችሁ ጥሩ ፤ የጠላታችን ጠላት ወዳጃችን ነዉ ፤ ያለንም ምርጫ በኤርትራ በኩል ብቻ ነዉ፤ (ይህንኑ አቋማቸዉን ከኮሚቴዉ ዉጭም በኮንፍረንስ ኮል ላይም ሳይቀር አንዱ አባላቸዉ በግልጽ ተናግሮታል) ወያኔን ብቻ አዉግዙ የሚል አቋም ስለያዙ፣

2ኛ ማንም ሰዉ የፈለገዉን የፖለቲካ ወይንም የሲቪክ ድርጅት አባል መሆን መብቱ ነዉ። ነገር ግን ከሃገርና ከሰራዊቱ ፍቅር የድርጅት ፍቅር በልጦበት ያለበትን የፖለቲካ ድርጅት ዓላማ ይዞ መጥቶ በዚህ ማህበራችን ላይ መጫን አይችልም። የማንኛዉም የፖለቲካ ድርጅት ሎሌ አንሆንም። አንድ ሠራዊት ከህዝብ የወጣና ለሀገርና ለሕዝብ የቆመ እንጂ የግለሰቦችና ወይንም የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አይሆንም ብለን የተስማማነዉን በመጣስ እኚህ መኮንን እና አብረዋቸዉ ያሉት አምስት ግለሰቦች የእገሌ ድርጅት ጠንካራ ድርጅት ነዉ ብዙ ደጋፊ አለዉ፣ የእገሌ ሚዲያ ብዙ ሰዉ ይደግፋዋል ,,,ስለዚህ ይህንን ድርጅት መደገፍ አለብን ወዘተ,,, የሚል አቋም ይዘዉ ስለመጡ።

3ኛ በአሁኑ የማህበራችን ሊቀመንበር በዛን ግዜ የግዚያዊ ኮሚቴ አባል በነበረዉ መኮንን አማካኝነት ረቆ ለዉይይት የቀረበዉ ወደፊት ለሚመሰረተዉ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ላይ እንወያይና ደንቡን አጽድቀን ማህበራችንን እናቋቁም ሲባል እነሱ የሚቋቋመዉ ማህበር እንዲመራ የሚፈልጉት እነሱ አባል በሆኑበትና በሚደግፉት የፖለቲካ ድርጅት ደንብ እንዲሰራ ስለሆነ በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ላይ ለመነጋገር ፈቃደኛ ያለመሆን አቋም ስለያዙ፣

4ኛ ራሱን ,,,,«የሰራዊቱ ድምጽ,,,» በሚል የሚጠራና (ከበስተኋላ ባለቤት ያለዉ ) የየትኛዉ ሠራዊት እንደሆነ በግልጽ ለመናገር የማይፈልግ ፣ በአንድ መኮንን አዘጋጅነትና በአንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪ ቁጥጥር ሥር ያለ ይህንን በሉ ፣ ያንን እንዳትሉ እየተባለ መመሪያ ተሰጥቶት በሚዘጋጅ የሬድዮ ሥርጭት የእኛ ልሳን መሆን አለበት። ይህንን የማይደግፍ ወያኔ ነዉ ወዘተ,,,,, የሚል አቋም በመያዛቸዉ።።

5ኛ በዚህ የተነሳ በተደጋጋሚ ሦስት የጊዚያዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ይህንን ለማቋቋም ያሰብነዉን ማህበር

ሀ- እነሱ ወስደዉ ሎሌ ሊያደርጉት የፈለጉት የፖለቲካ ድርጅት ስር ለማስገባት መሞኮሩ
ለ- እኛ የቀ/የኢ/የጦ/ኃይ/የፖ/ሠራዊት አባላት ስም እንደሌለን እኛ የምናዉቀዉ፣የማናፍርበት የምንኮራበት ስም እያለን የማናዉቀዉ ሠራዊት «,,,,የሠራዊት ድምጽ,,,,» የሚል ስም መስጠቱ፤
ሐ- ያለ ሻቢያ ምርጫ የለንም ፣ የሻቢያ ስም እንዳይነሳ ወዘተ,,,,,
መ- ተረቆ የቀረበዉ የመተዳደሪያ ላይ ለመወያየት ያለመፈለግ አለአግባብ መሆኑን በዉይይት ለማሳመን በተደጋጋሚ ብንሞክርም ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ፣ ከዛም በኋላ የስብሰባዉን መንፈስ ወደ እንካ ሰላምታ ስለሚቀይሩት ፈጽሞ በዚህ ሁኔታ መቀጠል የሚይቻል ደረጃ ላይ በመድረሱ፤

ዓለም አቀፍ  የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box  703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

6ኛ እንዲሁም ከዚህ አልፈዉ ተርፈዉ የኮሚቴዉ አባላት ከሆኑት  በቴሌኮንፍረንስ ላይ ሃሳብ ለመግለጽ የሚችሉት የሚፈልጉትን  ብቻ እንጂ ሌላዉ ሃሳቡን እንዳይሰጥ የመናገር ዕድሉን  በመዝጋት ፣ በአጋጣሚ ሃሳቡ ከነሱ,ጋር ካልሄደ ደግሞ እዝያዉ ቴሌኮንፍረንስ ላይ ማጣጣልና  ማዋርድ፤ሲሆኑ

ጉዳዩን በስፋት በመመልከት ከዚህ በላይ ምንም ማድረግ ስለማንችልና ልዩነታችንም መሰረታዊ ልዩነት እንዳለን ስለአረጋገጥን መፍትሔ ይዘን የተነሳነዉን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ብለን  የመተዳደሪያ ደንቡን አርቀን አዉጥተን ግንቦት 28/2014 እ,ኤ,አ, «ዓለም አቀፍ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ማህበር » ን በህጋዊነት አቋቁመናል።

ያሉን መሰረታዊ ልዩነቶችም ከዚህ እንደሚከተለዉ ናቸዉ፤

1ኛ) እነሱ እንደሚያምኑት ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ሃገራችን በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት ታሪክ እያላትና የዉጪ ጠላቶችዋ እንኳን ባልካዱበት ወቅት «,,,ኢትዮጵያ ከሁለተኛዉ ዓለም ጦርነት በኋላ የተፈጠረች ሃገር ነች,,,,» በሚል የወንበዴ ድርጅት ወይም በሻቢያ በኩል ብቻ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይመጣል፣ ሻቢያ ብቸኛ አማራጫችን ነው፣ ሻቢያ ነጻ ያወጣናል፣ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው፣ ሻቢያን  አትንኩ፣ ወያኔን ብቻ አውግዙ፣ የሚል አቃም አላቸው፣

እኛ ደግሞ

ሀ/ ሻቢያ የኢትዮጵያን ትንሣኤን ያመጣል፣ሻቢያ ነጻ ያወጣናል የሚል ቅዥት የለንም

ለ/ ወያኔን በአምሳሉ ጠፍጥፎ የሰራው ሻቢያ ነው ብለን እናምናለን።

ሐ/ በሻቢያና በህሀዋት መካከል የሥልጣን ሽኩቻ  እንጂ የአላማ ልዩነት አላቸው ብለን አናምንም።ስለሆነም ወያኔና ሻቢያ አንድም ሁለትም ናቸው እንላለን (መሪዎቹ ሁሉ ይነግሩናል።)

መ/ ከ 1993 የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በኃላ አዲስ አበባም አሥመራም ያለው  ሻቢያ ነው ብለን እናምናለን

ሠ/ ከዚህ ቀደም የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነኝ ብለው ሻቢያ ጉያ የገቡ ሦስት የፖለቲካ ድርጅቶች የገጠማቸው ዕጣ ፈንታ በሚገባ እናውቃለን።

ረ/ ከሁሉም በላይ ደግሞ የቀ/የኢ/የጦ/ኃይ/የፖ/ሠራዊት አባላት 17 ዓመታት ሙሉ የታገልንዉ የቆሰልነዉ ብሎም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መስዋዕትነት የከፈሉት ከዚህ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ጠላት ከሆነዉ ሻቢያ ከሚባለዉ ወንበዴ ድርጅት ጋር በመሆኑ በተለይም በ1983ዓ,ም, ጦርነቱ አብቅቶአል፣ ዕጃችሁን ስጡ ! ተብለዉ በገዛ አዛዦቻቸዉ ትዕዛዝ ተሰጥቶአቸዉ በሰላም መሳሪያቸዉን አስቀምጠዉ ዕጃቸዉን የሰጡትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የቀ/የኢ/የጦ/ኃይ/የፖ/ሠራዊት አባላትን ሰብስበዉ በዙ23 የአየር መቃወሚያ ጥይት የረሸነና ነፍሳቸዉ ያልወጣዉን በመቶዋች የሚቆጠሩትን ወንድሞቻችንን ታንክ በላያቸዉ ላይ የነደባቸዉ አስከሬናቸዉን ነዳጅ አርከርክፎ ያቃጠለ ፣ በቃላት ለመግለጽ የሚከብድ ኢሰብአዊ ፣አረመኔ ድርጊት ከጄኔቫ ስምምነት ዉጪ በሆነ መንገድ ወንድሞቻችንን የፈጀ ፣ ዛሬም ድረስ በሺህ የሚቆጠሩ የሠራዊታችን አባላትን ከመሬት በታች እስሮ በረሃ ላይ መንገድ እያስራ በሲኦል እንዲኖሩ ካደረገ  የወንበዴ ድርጅት ጋር አብሮ ለመስራትና ነፃ ያወጣናል ብሎ ለማሰብ ፣ ብሎም በተሰዉት ሰማዕታት መስዋዕትነት ላይና በስቃይ ላይ ባሉ ወንድሞቻችን ሰቆቃ ላይ ተረማምደን ከሻቢያ ጋር የምንዳራበት አዕምሮ የለንም።

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

2ኛ) እነሱ ማህበሩን ወስደዉና ስበዉ የእነሱ የፖለቲካ ድርጅት ሎሌ አድርገዉ ድርጅታቸዉ ምድር ጦር ፣አየር ኃይል ፣ ባህር ኃይሉና የፖሊስ ሠራዊት በዕጃችን ነዉ ያለዉ ብለዉ በወደቁት ሰማዕታት አጽምና እኛም በህይወት ባለነዉ ስም ለመነገድና ድርጅታቸዉን አገዝፈዉ ለማሳየት የገንዘብ መሰብሰብያ ለማድረግ ነዉ።

እኛ ደግሞ

እኛ ያለስማችን ስም፣ ያለ ስራችን ስራ፣ ተሰጥቶን የደርግ ወታደር ፣ ኢሠፓ ወዘተ,,,, እየተባልን አንገት ደፍተን ከደረሰብን የህሊና ቁስል ገና ሳናገግም እንደገና እንዚህ ግለሰቦች የፖለቲካ ድርጅት ፣የፖለቲካ ትርፍ ፣የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ፣ የቀድሞዉ ሠራዊት በእጄ ነዉ ብለዉ ለሌላ ዙር የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘመቻ ሲባል ለሚደረገዉ ትያትርና ድራማ ተባባሪ መሆን ስለማንፈልግ። የእነሱም የፖለቲካ ድርጅት ሎሌ ሆነን የእነሱ የድርጅት ታፔላ ተለጥፎብን ፣ የእነስ ፖለቲካ ሲከስም አብረን ልንከስም ፣ የእከሌ ጦር ፤ወታደር ልንባል ፈቃደኛ አለመሆናችን ነዉ። የወጣነዉ ከህዝቡ ነዉ ፣የምንቆመዉ ለህዝቡ ነዉ ፤ ይህ የእኛ ብቻ ሳይሆን የማንኛዉም ሀገር የመከላከያ ሰራዊት አቋም ነዉ ብለን እናምናለን፣

3ኛ) እነሱ በድርጅታችዉ ልሳን ስር ገብተን የእኛ ልሳን ,,,,,,,«የሰራዊቱ ድምጽ»,,,,,, የሚባል እንዲሆን ሲያምኑ፤

እኛ ደግሞ

ሀ/ የምናፍርበት ሳይሆን የምንኮራበት ፣ የማያሻማ ሳይሆን በግልጽ የተቀመጠ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት የሚል ስም እያለን፣ በምን ሂሳብ ስም እንደሌለዉ የማንነቱ ያልታወቀ የሠራዊቱ ድምጽ ልሳን እንደተፈለገ ሚስጥሩ ስላልገባን ይህንንም ስለምንቃወም ፣

ለ/ ይህ ,,,«የሠራዊቱ ድምጽ »,,,, ተብዬዉ ፍጹም ነጻ ሚዲያ ያልሆነ ፣ ነገር ግን የእኛ ልሳን እየተባለ እኛ መተዳደሪያ ደንብ አዉጥተን በእኛ ስር የማይሰራ የማይታዘዝ , በሃያ አንደኛዉ ክፍለዘመን ሻቢያ እንዳትሉ ፣ይህን በሉ ፣ያን አትበሉ እየተባለ በድርጅት መመርያ የሚታዘዝ ነገር,ግን በእኛ ስም የሚነገድበት በመሆኑ፣

ከሁሉም በላይ የሚያስገርመዉ የቀ/የኢ/የጦ/ኃይ/የፖ/ሠራዊት አባላት ለ17 ዓመታት ሙሉ ያታገለትና መስዋዕትነት የከፈለዉ ከወያኔ ብቻ ሳይሆን በዋናነት ከሻቢያ ጋር መሆኑ እየታወቀ ፣ በዚህ ሬድዮ ፕሮግራም ስለሻቢያ ካልተናገረ ምን ለነገር እንደሚችል በጣም ዕንቆቅልሽ ነዉ። እነዚህ ግለሰቦች የገንዘብና የድርጅት ፍቅር ዓይናቸዉን ካላወረዉ ይህንን ያጡታል ብለን አናስብም።

ለማጠቃለል ያለን ልዩነት በአጭሩ ይሆንን ይመስላል፤ ለወደፊቱም እንዚህ ግለሰቦች ቆም ብለዉ ማሰብ ካልቻሉና ከዚህ አፍራሽ ተግባራቸዉ ሳይቆጠቡ በዚህ ከቀጠሉ በእኛ በኩል በዝርዝር ማስረጃ የተደገፈና የእነዚህን ግለሰቦች ማንነትና ተግባር ከማጋለጥ ወደኋላ

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

አንልም። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከእነዚህ ግለሰቦች የተሳሳተ መንገድ አብረዉ የሚሄዱትን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ቆም ብለዉ እንዲያስቡና ልቦና እንዲሰጣቸዉ እያሳሰብን ማህበራችንን ለማፍረስ ከሚደረግ ጥረት በስተጀርባ ሻቢያና እነማን ከኋላ እንዳሉ ዓይናቸዉን ገልጠዉ እንዲያዩ እናሳስባለን።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት ከህዝብ የወጣ ለህዝብ የቆመነዉ!!!!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!!!!

ዓለምአቀፍ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ማህበር

ግልባጭ

- ለምድር ጦር መረዳጃ ማህበር ዋሺንግተን ዲሲ

-ለአየር ኃይል መረዳጃ ማህበር ዋሺንግተን ዲሲ

-ለባህር ኃይል መረዳጃ ማህበር ዳላስ ቴክሳስ

-ለፖሊስ ሥራዊት አባላት በያሉበት